# <u>አንድ ጥያቄ ለታክሎ ተሾመ!</u>

እጅግም ባልበሰለው ጽሁፍ  የማርቀቅና የማዋቀር ችሎታዬ ዳዴ ለማለት ወደመድረክ ብቅ ብል አያምርብኝም ብዬ አላስብም:: ምክንያቱም የበሰለ የስነጽሁፍ ሞያና ችሎታ ይዘው ነገር ግን አደራቸውን መወጣት ሳይችሉ ከሚቀሩ አልያም ታሪክን ያለታሪክነቱ ሲመጥኑት ከማየት የሚበልጥ ምንም የማያምር ነገር አይኖርም ብዬ አስባለሁና ::

ታሪክ ሊሞትና ዘመን ሊሽረው የማይችል ቋሚ ቅርስ ነው። እውነትም ነው ታሪክን የሚሰራ ደግሞ ምን ያህል የላቀ እንደሚሆን ምስክር አያሻውም። ማንም ሠው ለየተሰለፈበት ዘርፍ የባለታሪክነት ባለአደራ ድርሻ አለው እኔም የቆምኩለትና ያለፍኩበት ሠፊ ታሪክ የድርሻዬን ያህል እንድትጠበቅልኝ ባለአደራ ነኝ:: ስለዚህ አልፎ አልፎም ቢሆን ለፖለቲካ ጥቅም ሲባል የታሪክ መዛባት በጸሀፊያን ዘንድ እየተለመደ የመጣ ቢሆንም በጣም የሚያመኝን ሁኔታ ግን ማለፍ አቅሙን ስለማጣ አንድ ለማለት እነሆ እጄን አነሳሁ::

ድሮ ድሮ  ልጅ ሳለሁ በሰፈራችን በጣም የሚታወቅ መልኩ የሚያስፈራ ነገር ግን የሚሊቴሪ ዩኒፎርሙን ሲለብስ ደሞ ከአረማመዱና ከወታደራዊ ሥርዓት አክባሪነቱ ጋር ልዩ ግርማ የነበረው ኃይሉ ትርፌ የሚባል ልጅ ነበረ ።ኃይሉ ወታደርነት ያምርበታል።  ስለወታደርነቱ ሲናገር ደሞ  እኔ ወታደር ነኝ ከሚል ይልቅ ባለ አደራ ነኝ ማለትን ይወድ ነበር ።: ሙሉ ቃሏንም የወረሰው ወታደር ከነበሩ አባቱ እንደሆነ አዘውትሮ ይናገር ነበር። << የሀገር ባለአደራ ! >> እኔም የባለ አደራ ወታደር ልጅ እንደመሆኔ  ሀገሬን ጠባቂ የሀገር ባለ አደራ ነኝ ሲል የማይበት መንፈሰ ጠንካራነት አሁንም ድረስ ሲታወሰኝ ይኖራል። ኃይሉ ትርፌን እንደው አነሳሁት እንጂ የባለአደራነት ቃል የሚረጋገጥባቸው ኢትዮጵያውያን በተለይም የታሪክ ባለአደራዎች ፀሀፍት(ደራሲያን)፣ ጋዜጠኞች፣ መምህራን፣የፖለቲካ መሪዎች፣ ወታደሮች፣ ታጋዮች ወዘተ ቀዳሚዎች ናቸው ::

በቀደሙት ዘመናቴ መጻህፍት ሙሉ ለሙሉ ትክክለኛ ዋቤ ስለመሆናቸው ምንም ጥርጣሬ አይገባኝም ነበር። ይሁን እንጂ ድሮ ውሸት አልነበረም ማለቴ ግን አይደለም:: ለመጀመሪያ ግዜ ሙሉ በሙሉ በደንብ አድርጌ ያነበብኩት መጽሃፍ << አ ሠላም በስምሽ ስንት ግፍ ተሠራ>> የሚል ነበር:: የዚያች መጽሃፍ ስሜት ያሳደረብኝ ተጽእኖ ቀላል አልነበረም። ተፈጥሮና መብት ምን እና ምን መሆናቸውን እንድመረምር ያደረገቺኝ መጽሃፍ ስለነበረች አሁንም ድረስ ውስጤ አለች። ከዚያም ማንበብ ያደረገልኝ እገዛ ዲሞክራሲያ ላይ ደርሶ ወደ ትግል መራኝ የነ ጥላሁን ግዛው፣ የነማርታንና ዋለልኝ መኮንን የተማሪዎች የትግል እንቅስቃሴ ምክንያት በማድረግ በየትምህርት ቤቱ የዲሞክራሲ ፍም እንዲቀጣጠል በራሪ ወረቀቶችን ለንባብ ከማብቃት ጀምሮ የዲሞክራሲያን ብርሀን በመላው ሀገሪቱ አብርቶ ለማሳየት በሚደረገው ሥር ነቀል ትግል አደራውን የተወጣ ባለታሪክ ወጣት አንዱ ስለነበርኩ አሁንም ድረስ ኩራቴ ነው። አይቼዋለሁና ነበርኩበትና ያንን ዘመን ብዘክር የሚያስዋሽኝ አልያም የሚያስነቅሰኝ  አንዳችም ምክንያት አይገኝም ሞት እንኳ እንዳላሸነፈኝ ታሪክ ምስክር ነውና::

በኢትጵያ የዴሞክራሲ ትግል ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ለህዝቡና ለወገኑ ራሱን አሳልፎ ሰጦቷል:: በዚህም እጅግ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ታጋይ ወጣት በሀገራችን ታሪክ ውስጥ መቼም ድረስ ሊረሳ የማይችል የታሪክ ሥፍራ ይዟል::

በአፋኙና በፋሺስቱ የደርግ ሥርዓት ከሠው ልጅ ሕሊና ውጪ በሆነ ግፍ ህይወታችውን መሥዋዕት ላደረጉ፣ በከፍተኛ ሥቃይ አካላቸውን ላጡና ሠዋዊ ሥብዕናቸውን ተገፈው ከትምህርት እድል ከሥራና ከተለያዩ መብቶች ታግደው ህይወታቸውን በከንቱ እንዲያሳልፉ የተገደዱት ኢትዮጵያውን ለነጻነት ናፋቂው የኢትዮጵያ ህዝብ ባለውለታዎች መሆናቸው ልዩ ማስረጃ አያሻውም።

በተለይም ደግሞ በአረመኔው የደርግ አገዛዝ የተጨፈጨፈውን ምሁር ወጣት በታሪክ ለመዘከር በሚታተሙ አንዳንደ መጻህፍት ስንመለከት ምን ተሺ መጻህፍትን ዋቤ አድርገው የደም ዘመን ብለው የጻፉትን መጽሀፋቸውን ለንባብ ያበቁ ደራሲ ታክሎ ተሾመን አንድ ጥያቄ እንድጠይቃቸው ግድ ብሎኛል::

1ኛ/ የኢትዮጵያን ህዝብ የፍትህና የዴሞክራሲ ጥያቄ ለማረጋገጥ እንደሻማ የቀለጡና መስዋዕት ከሆኑ ጓዶች ስም ውስጥ የአንዷት ጓድ ስም በትክክል አልተጻፈም፡፡

በደንብ አውቃታለሁ መርዓተ አሥግድ ትባላለች ፡ በፓርቲው ዲሲፕሊን የታነጸች ለቆመችለት ዓላማ ጽኑ እና ደፋር ታጋይ ነች አስታውሳለሁ። በሰኔ ወር ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ዓመተምህረት ከታጨቅንበት ወህኒቤት አንዱን ቀን በህዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ለጥያቄ ትፈለጋላችሁ ተብለን ከተወሰድን በኋላ ከተደረደርንበት ኮሪዶር ፊለፊት ባለው ክፍል ውስጥ መጀመሪያ ለጥያቄ የተጠራችው እሷ ነበረች ትዝ ይለኛል ከነበሩት ሶስት መርማሪዎች ውስጥ ተስፋዬ የሚባል መርማሪ ገና ሳትቀመጥ እንዲህ አላት "ከአንቺ ጋር ምንም ጥያቄና መልስ አያስፈልገም ጸረ ህዝብ ነኝ በይና ራስሽን አጋልጪ" ሲላት "ጸረ ህዝብ አንተ ነህ ! የጭቁኑን የኢትዮጵያን ህዝብ ደም የምትመጥ ፋሺስት አንተነህ እኔ ለዴሞክራሲና ለነጻነት የቆምኩ የድሃው የኢትዮጵያ ልጅ እንጂ ጸረ ህዝብ አይደለሁም" ስትል በታላቅ ኃይል ተናገረችው ....... ይሄኔ በውስጣችን የነበረው ስሜት ጉልበትን አገኘ፡፡

ወዲያው ጥንብ እንዳገኘ ጅብ ለሶስት ተረባረቡባት በመሃሉ እናቸንፋለን እያለች የምታሰማን ቃል ሁላችንም ባለንበት እንድንደግመው አድርጎናል። ከዛም ራሷን ስታ ወደቀች ከቡጢና ከእርግጫ የተረፈችውንም ሰቅለው ባላቸው ጉልበት ሁሉ ሲደበድቧት ዋሉ። ወደ ወህኒ የመለሱን ሰው እንዳያይ በምሽትና በቃሬዛ ነበር፡፡

መርዓተም እስከተገደለችበት ቀን ድረስ ባደረሱባት ድብደባ ምክንያት ክፉኛ ትሠቃይ ነበር። ያም ሆኖ ሻል ባላት ጊዜ ሁሉ እናቸንፋለን ማለትን አትረሳም፡፡ በመጽሃፍዎ ተሳስቶ የተጻፈው ስሟ ይስተካከልልኝ ይሆን ብዬ በቁጭት መርዓተ አሥግድን አስታወስኳት፡፡

2ኛ/ ከ1968 ጀምሮ ነገሌ አካባቢ በመኢሶን በሰደድ በኢጭአትና በወዝሊግ ጥበቃ ጓዶች ከተገደሉት መካከል ብለው በገጽ 414 ካቀረቡት መካከል በአንድ ጀምበር ብቻ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ የተጨፈጨፉት 16 ሲሆኑ እርስዎ ከአስራ ስድስቱ ሁለቱን ብቻ ለዚያውም አንዱን ትክክል ባልሆነ ስም የጠቀሱት ለምን ይሆን ? አልኩና የቁጭት ጥያቄ ውስጥ ገባሁ ከሆነም **ደሞ በዋቤነት ካቀረቡት እና ካነበብኩት አንዱ መጽሀፍ ውስጥ ሁሉም በትክክል ከነታሪካቸው ተጽፈው ሳለ የእርስዎ ሁለቱን ብቻ መቆንጸል እና ማቅረብ**

**ለምን አስፈለገዎ ?** ታሪክን ማጉደል አይሆንብዎትም? ወይስ የመስዋትነትን ታሪክ በዘንድሮ ፖለቲካ መተርጎም? መልሱን ከእርስዎ እጠብቃለሁ።

ጥያቄዬን ላይመልሱልኝ ቢችሉ እጅግም አልከፋም ምክንያቱም ሌሎች ጸሃፊዎች ጥሩ አድርገው ጽፈውታልና ነው። ወደፊትም ይጽፉታል።

እኔ እስከማምነው ድረስ  ማንኛውም የታሪክ ጸሀፊ ድርብ አደራ አለበት። የታሪክ አደራ የእውነተኛ ምስክርነት አደራ፣ የፍርድ አደራ፣ የሀገር አደራ፣ የህዝብ አደራ፣ የትውልድ አደራ . . . ወዘተ  ፡፡

ውድ ደራሲ ታክሎ ያቀረቡት እኮ በራሪ ፓምፕሌት አይደለም መጽሀፍ ነው። መጽሀፍ ደግሞ ቋሚ ነው። ሲዳሞ እከሌ የሚባል ልጅ ተገድሏል ጎጃም ደሞ እንትናና እከሌ የሚባል ወዘተ የሚል ዝም ብሎ ታሪክ የለም። እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ወጣት ከንቱ አልሞተም:: እያንዳንዱ የተሰዋ ወጣት ለሀገሩና ለህዝቡ ፍትህና ዴሞክራሲን ያለገደብ ለማስገኘት ባደረገው ፍጹም እውነተኛ ትግል የተሠዋ ነው። ባጭሩ ከጽሁፍዎ እንደተረዳሁት በትግል የተሠዉ የፍትህ እና የዴሞክራሲ ታጋዮች ፍጹም በተዘበራረቀ ሁኔታ ነው የቀረቡት። ነጌሌ አካባቢ የተገደሉ ይሉና በዚያው ርዕስ ሥር ጅጅጋ ሄደው ደሞ አንድ ታጋይ ያሳዩናል። ታሪክ እንዲህ ይጻፋል እንዴ?  የእርስዎን መጽሀፍ ዋቤ አድርጎ የሚጽፍ ሌላ ጸሀፊ ደግሞ ምን ዓይነት ስህተት ሊሰራ እንደሚችል ማሰብ አይከብድም።ታሪክ ለእራስ ታዋቂነት ባሻገር እውነታነቱ፣ ቅርስነቱ፣ ታሪክነቱ ሊታይ ይገባል። ለእራስ ጥቅም ተብሎ ተዛብቶ የተፃፈ ታሪክ ለሃገራቸው ሲሉ የሞቱትን ድጋሚ መግደል ነው።

ምናልባት የስም መዛባት እንደቁምነገር ላይቆጠር ይችላል ብለው ቢገምቱ እንኳን ስህተት መሆኑን ግን እኔ ሳልናገር ማለፍ አቅቶኛልና እርስዎም ቅር እንደማይሰኙብኝ አምናለሁ። በዛ ወቅት የነበርን የአካባቢው ነዋሪዎች ገና በሕይወት የተረፍን አለንና ምስክርነታችንን ለመስጠት ወደ ኋላ አንልም።

መጽሐፍ ታሪክ ነው። ለባለታሪኩ ደግሞ ጸሃፊያን ባለአደራ ናቸው ስለዚህ ጸሃፊያንን አደራ እላለሁ! ወያኔ በትግል ዘመኑ የእያንዳንዱ የትግራይ ነዋሪ ህዝብ ቤት በር ተንኳኩቷል ይላል። በኢሕአፓ የፍትህ ትግል ውስጥ ግን የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤት በር ተንኳኩቷል !

እናቸንፋለን

መስፍን መሀመድ ከ አዶላወዩ
mesfinadola@gmail.com